# የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓት

**ዝናሽ ሰለሞን[1]፣ ዘሪሁን አስፋው[2] እና የወንድወሰን አውላቸው[3]**

**አጠቃሎ**

ይህ “የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓት” ጥናት በሀድያ ብሔረሰብ ባህል ከዕለተ ሞት አንስቶ እስከ ሀዘን ማብቂያ ባሉ መዋቅራዊ ሂደቶች የሚከወኑ ልዩ ልዩ ሥርዓተ ከበራዎችን በመተንተን የሀገረሰቡን ልማድ፣ እሴቶችና ማህበራዊ ግንኙነቶች ለመግለጽ ያለመ ነው፡፡ ከሰው ልጆች የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓቶች አንዱ የሆነውን ሞት ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ የሀዘን ሥርዓቶች በባህሉ የተደነገጉ ሥርዓቶችንና ሂደቶችን የተከተሉ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት አቢይ የምርምር ጥያቄም በሀድያ ብሔረሰብ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚከወኑ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትና ለምንስ ይከናወናሉ? የሚል ነው፡፡ ለእነዚሁ ምላሽ ለመስጠት ስነሰብዓዊ ፈለግን መሠረት ካደረጉ የባህል ጥናት ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ ክዋኔያዊ እና ዐውዳዊ ንድፈ ሀሳቦች አገልግለዋል፡፡ የጥናቱ መረጃዎች “የሀድያ ብሔረሰብ የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥርዓተ ከበራዎች” ላይ እየተካሄደ ለሚገኝ ምርምር ከ2012 እስከ 2014 ዓ/ም በአካባቢው በሀድያ ዞን በተከናወነ የመስክ ሥራ በተሳታፊ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎችን በተዛማጅ ጽሑፎች በማጠናከር በገላጭና ፍካሬያዊ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው እንደተመለከተው የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ሞትን ማወጅ/የለቅሶ ጥሪ (አረዲማ)፣ ቀብር፣ የማጽናናት/የማስተዛዘን ሥርዓት (በካሪማ) እና የሀዘን ማብቂያ (ጋባ) የሚባሉ ሂደቶችንና ሥርዓቶችን ያካትታል፡፡ በእነዚህ ሂደቶች የሚፈጸሙ ሥርዓቶች ከሟቾች እድሜ፣ ፆታና ማህበራዊ ደረጃዎች አንጻር እንደሚለያዩ ታይቷል፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው በሀድያ ብሔረሰብ የሚከወነው የሀዘን ሥነ ሥርዓት የዘወትር/የተራ ሰው እና የታዋቂ ሰው በሚል በሁለት ይከፈላል፡፡ የዘወትር ሞት በበኩሉ የህጻንና የወጣትና የጎልማሳ በሚል ይፈረጃል፡፡ የታዋቂ ሰው ሞት በጦርነት፣ በልማት፣ በበጎነት በመሳሰሉት በአርዓያነት የሚጠቀሱ ጀግኖች፣ የጀግና ሚስቶች እና የእድሜ ባለጸጎች ሞትን የሚመለከት ሲሆን በባህሉ የተደነገጉ ልዩ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች የሚፈጸምላቸው ናቸው፡፡ በሀድያ ብሔረሰብ ለማህበራዊ ሕይወት መጠናከር ጉልህ ፋይዳ ካላቸው ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች አንዱ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ሲሆን በእያንዳንዱ ሂደት በስነቃል፣ በቁስና በክዋኔ የሚተላለፉ መልዕክቶች የሀገረሰቡን ባህልና ታሪክ ለትውልድ የማሸጋገር እና ባህላዊ እሴቶች እንዲጠበቁ የማጠናከር፣ የማስተማርና የመቆጣጠር ተግባር እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** ሞት፣ ሀዘን፣ የሽግግር ሥነ ሥርዓት፣ ክዋኔ

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ፒ ኤች ዲ ተማሪ zinashsolomon8@gmail.com
[2] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር እና የጥናቱ አማካሪ የነበሩ
[3] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር እና የጥናቱ አማካሪ yawlachew@gmail.com

## 1. መግቢያ

የሥነ ሥርዓትን (Ritual) ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ ከነዚህ መካከል Gennep (1960፡2-3) ሥነ ሥርዓት ከአንድ የዕድሜ ደረጃ ወደሌላ መሸጋገርን ምክንያት በማድረግ የሚከበር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ Bell (1997፡171) ደግሞ ሥነ ሥርዓት ማህበራዊ ልማድን፣ ታሪካዊ ተግባራትን እና በየዕለቱ የሚደጋገሙ ክንውኖችን እንደሚያካትት ይገልጻሉ፡፡ Sims and Stephens (2005:95) በበኩላቸው ሥነ ሥርዓቶች ተደጋጋሚ፣ በሥርዓት የተዋቀሩ፣ ቁጥጥር ያለባቸው እና ብዙውን ጊዜ በአንድ ቡድን ውስጥ ያለን አባልነት የሚያመለክቱ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ Dorson (1972፡159) ሥነ ሥርዓቶች በዋናነት ከአንድ ወቅት ወደሌላ ወቅት እንዲሁም ከአንድ የሕይወት ዑደት ወደሌላው መሸጋገርን የሚያመለክቱ ሲሆኑ ከነዚህ ማህበራዊ ክስተቶች መካከል የሕይወት ዘመን ሽግግር አበይት ክፍሎች ወሊድ፣ ጋብቻ እንዲሁም ሞት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ከብያኔዎቹ በመነሳት ሥነ ሥርዓቶች የተወሰኑ ቡድኖች የሚያዘጋጁትና የሚሳተፉበት ከወትሮው ለየት የሚሉ ማህበራዊ ክስተትና አጋጣሚን ለማብሰር የሚዘጋጁ ክበራዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

Bell (1997:94-132) እንደሚሉት የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች በስድስት ይመደባሉ፡፡ እነዚህም የሕይወት ዘመን ሽግግር፣ ዓመታዊ፣ መስዋዕት ማቅረቢያ፣ ከበሽታ ለመፈወስ የሚፈጸሙ፣ ጾምን ተከትለው የሚመጡ እና ፖለቲካዊ ናቸው፡፡ ከነዚህ የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች መካከል የሕይወት ዘመን ሽግግር (Rites of passage) አንዱ ሲሆን እንደ ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት ያሉና በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱ ታላላቅ ዑደቶችን ተከትለው በየባህሉ የሚደረጉ ሥነ ሥርዓቶች ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ከነዚህ ስድስት የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች መካከል የሕይወት ዘመን ሽግግር ላይ ያተኩራል፡፡ ነገር ግን ከሀዘን ሥነ ሥርዓት ውጪ ያሉትን ሌሎች የሽግግር አይነቶች አይመለከትም፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ በሀድያ ብሔረሰብ ባህል ከዕለተ ሞት አንስቶ እስከ ሀዘን ማብቂያ ባሉ መዋቅራዊ ሂደቶች የሚከወኑ ልዩ ልዩ ሥርዓተ ክበራዎችን በመተንተን የሀገረሰቡን ልማድ፣ እሴቶችና ማህበራዊ ግንኙነቶች መግለጽ ነው፡፡ በጥናቱም በሀድያ ብሔረሰብ ከሞት ጋር በተያያዘ የሚከወኑ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትና ለምንስ ይከናወናሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል፡፡

ጥናቱ በርዕሰ ጉዳይና በቦታ የተወሰነ ነው፡፡ ርዕሰ ጉዳይን በተመለከተ ከሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓቶች መካከል አንዱ የሆነውን የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔን መግለጽና መተንተን ላይ ያተኩራል፡፡ ቦታን በተመለከተ አላማ ተኮር ንሞናን ተግባራዊ በማድረግ የማህበረሰቡን የሀዘን ሥነ ሥርዓት በተመለከተ ተገቢውን መረጃ ለማግኘትና የመረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥ ወካይ በሆኑ አራት ወረዳዎች ማለትም ሌሞ፣ ሶሮ፣ ምስራቅና ምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳዎች ላይ ይሆናል፡፡

### 1.1. የሀድያ ብሔረሰብ አካባቢያዊና ማህበረ ባህላዊ ዳራ

ሀድያ ዞን በአስር ወረዳዎችና በአንድ የከተማ አስተዳደር እንዲሁም በ 323 የገጠር ቀበሌዎች የተደራጀ ነው። የዞኑ ዋና ከተማ ሆሳዕና ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ 205 ኪሎሜትር ላይ ይገኛል። ሀድያ ዞንን የተለያዩ ወረዳዎችና ልዩ ወረዳዎች ያዋስኑታል። እነሱም በስተሰሜን ጉራጌ፣ በሰሜን ምስራቅ ስልጤ፣ በደቡብ ወላይታ፣ በምስራቅ ከንባታ፣ በምዕራብ ጊቤ ወንዝና የም ልዩ ወረዳ ናቸው (Solomon 2008፡1-3)።

በሀድያ ማህበረሰብ አካባቢ የሚታወቁ የተለያዩ ሥርዓተ ከበራዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ነው። የአከዋወን ሂደቱም በእድሜ ደረጃና በጀግንነት ይለያያል።

በሀድያ ብሔረሰብ የዕድሜ ደረጃን የሚያመለክቱ የተለያዩ ስያሜዎች ይገኛሉ። የሰው ዕድሜ በደረጃ የሚመደብ ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃም በተለያየ ስያሜ ይታወቃል። አንድ ህጻን ልጅ ከተወለደ እስከአራት አመቱ ጪሊቾ (ለወንድ)፣ ጪሊቼ (ለሴት) ተብሎ ሲጠራ ከ5-11 ዓመት ኦሺቾ (ለወንድ)፣ ኦሺቼ (ለሴት) ተብሎ ይጠራል። ልጆች በወጣትነት የእድሜ ክልል ከ18-29 ወራድቾ (ወንድ)፣ ባጃሜ (ሴት) ይባላሉ። በሌላ በኩል ሰዎች የወጣትነት እድሜያቸውን ጨርሰው ትዳር ሲመሰርቱ ወንዱ መንቾ ሴቷ ሜንትቼ ተብለው ይጠራሉ። በእድሜ ገፋ ያሉት ደግሞ ወንዱ ሎመንቾ ሲባል ሴቷ ሎመንቼ ተብለው ይጠራሉ (አለባቸውና ሳሙኤል። 2002፣ 235-236)።

ከላይ የተዘረዘሩ የእድሜ ልዩነቶች የሀዘን ሥነ ሥርዓት የአከዋወን ሂደቱን የተለያየ እንዲሆን ያደርጋሉ። አቶ መንገሻ ገበየሁ እንደሚሉት "የእድሜ ባለፀጎች (ከ80 በላይ) መሞታቸው የሚጠበቅ ስለሆነ ቢሞቱም በሕይወት እያሉ መስራት የሚገባቸውን ሰርተው ነውና የሞቱት አረፉ እንጂ ሞቱ አይባልም።"[4] በመሆኑም ከሞቱ በኋላ በአካል አንድ ላይ እንዳሉ እንዲታሰብ የሚቀበሩት በመኖሪያ ቤታቸው ፊት ለፊት በሚታይ ቦታ ነው። የሟች ቤተሰቦችም ሲወጡ ሲገቡ የመቃብር ሥፍራውን እያዩ አብረው እንዳሉ ያስባሉ።

በሀድያ ብሔረሰብ አባላት ዘንድ ቀደም ባሉ ጊዜያት ጀግና ተብለው እውቅና የሚሰጣቸው ሰዎች በጦር ሜዳ ያሸነፉ፣ በአደን ወቅት አንበሳና ሌሎች የዱር እንስሳትን የገደሉ ሰዎች ሲሆኑ ጀግንነታቸውን ለማሳየት በእጃቸው ጋሻ (አጊራ) ይይዛሉ። ጆሮአቸውንም ተበስተው ሎቴ ያንጠለጥሉ ነበር።[5]

አሁን ባለው ሁኔታ በብሔረሰቡ ዘንድ ጀግና የሚባሉ ሰዎች የደጃችነት፣ የአንጃችነት እና የገራድነት ስልጣን ያላቸው የጎሳ መሪዎች ናቸው። ሹመቱ የሚሰጣቸው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ላላቸውና ነገሮችን አመዛዝነው መፍታት ይችላሉ

[4] አቶ መንገሻ ገበየሁ እና አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ/ም)።

[5] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 22 ቀን 2012 ዓ/ም)።

ተብሎ ለሚታመንባቸው ነው፡፡[6] እነዚህ ተሿሚዎች በአካባቢው የተለያዩ ግጭቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ይታወቃሉ፡፡

ማህበረሰቡ ጀግና ያላቸው ሰዎች በሞት ሲለዩ የሚከወነው የሀዘን ሥነ ሥርዓት ከተራው ሰው የተለየ ነው፡፡ የቀብራቸው ዕለት በሕይወት እያሉ ይለብሷቸው የነበሩ አልባሳትና መገልገያ ቁሶች ወደማስለቀሻ ሜዳ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ከነዚህ መካከል ካፖርት፣ ፈረስ፣ ጦር፣ ጋሻ፣ የነብር ቆዳ ይጠቀሳሉ፡፡[7] ለቀስተኞቹም ቁሶቹን እያዩ የሚቾቹን ጀግንነት እያስታወሱ ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡

በሀድያ ማህበረሰብ ሰዎች በሞት ሲለዩ የሚከናወኑ የተለያዩ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም የዚህ ጥናት ትኩረት በመሆናቸው በቅደም ተከተል ተተንትነው ይቀርባሉ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱን ጽንሰ ሀሳቦች የያዘ ሲሆን ሁለተኛው የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ ሦስተኛው ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ነው፡፡

### 2.1. የፅንሰ ሀሳብ መሰረቶች

ከጥናቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጽንሰ ሀሳቦች ማለትም የሥነ ሥርዓት ምንነት፣ የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓት እንዲሁም ሞትና ሀዘን ተገልጸዋል፡፡

### 2.1.1. ሥነ ሥርዓት (Ritual)

የሥነ ሥርዓትን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ ከነዚህ መካከል Dorson (1972፡159) ሥነ ሥርዓቶች በዋናነት ከአንድ ወቅት ወደሌላ ወቅት እንዲሁም ከአንድ የሕይወት ዑደት አበይት ክፍሎች ወደሌላው ሽግግር የሚደረግበትን ሁነት የሚያበስሩ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ Bell (1997፡171) ሥነ ሥርዓት ማህበራዊ ልማድን፣ ታሪካዊ ተግባራትን እና በየዕለቱ የሚደጋገሙ ክንውኖችን እንደሚያካትት ይገልጻሉ፡፡ Mazama and Asante (2009፡575) ደግሞ ሥነ ሥርዓት መንፈሳዊ ድርጊቶች የተሸከሟቸውን ጉዳዮች የሚገልጽ ሲሆን ማህበረሰቡ በሚሰጠው ዕውቅና መሠረት ሁልጊዜ በማክበር በድግግሞሽ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ከላይ የተገለጹ ብያኔዎች የሚያስረዱት ሥነ ሥርዓት ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደሌላ ሽግግር በሚደረግበት ወቅት የሚደረጉ ማህበራዊ ልማዶችን እና በየዕለቱ የሚደጋገሙ ክንውኖችን የሚያካትት ሲሆን እነዚህ ክንውኖች በድግግሞሽ የሚከወኑ በመሆናቸው የግለሰብ ብሎም የማህበረሰብ መለያ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በሀድያ ብሔረሰብ ከሕይወት ዘመን ሽግግሮች አንዱ ከሆነው ሞት ጋር በተያያዘ

[6] አቶ ኤሊያስ አሬቦ፣ ቃለ መጠይቅ (መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[7] አቶ አየለ ኡራጎ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥር 27 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

የሚከወኑ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች እንዴት እና ለምን እንደሚከወኑ በማጥናት የማህበረሰቡን ማንነትና የሚኖሩበትን አካባቢ ለመግለጽ ታስቧል፡፡

### 2.1.2.. የሕይወት ዘመን ሽግግር (Rites of passage)

የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓቶች ሰዎች ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላ መሸጋገራቸውን የሚያመለክቱ ሲሆኑ እነዚህ ለውጦች የቦታ፣ የሁኔታ፣ የማህበራዊ ደረጃ እና የእድሜ ለውጥን ተከትለው በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኙና ሽግግሩን ጠቋሚ በሆኑ የተለያዩ ሥነ ሥርዓቶች ታጅበው የሚከበሩ ናቸው፡፡ በነዚህ የሽግግር ሥነ ሥርዓቶች አማካይነት የሰው ልጅ ከአንድ የሕይወት ዑደት ወደሌላ እንዲሁም ከአንድ ማህበራዊና አካላዊ አቋም ወደሌላ መሸጋገሩን ያመለክታል (Gennep.1960፡2-3)፡፡

ሰዎች ሲወለዱ ከእናታቸው ማህፀን ተለይተው ይህንን ምድር የሚቀላቀሉ በመሆናቸው ሕይወትን አንድ ብለው መኖር ይጀምራሉ፡፡ ከዚያም የህጻንነት ዘመናቸው ሲያበቃ ወደ ልጅነት፣ የልጅነት ጊዜያቸው ሲያበቃ ወደወጣትነት፣ የወጣትነት ጊዜ ሲያበቃ ወደጎልማሳነት፣ ከጎልማሳነትም ወደ እርጅናና ሞት ይሸጋገራሉ፡፡ የሕይወት ዘመን ሽግግር ሁልጊዜም እንዲህ ባለ ዑደታዊ ክንውን የተሞላ ነው፡፡ በመሆኑም የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓት ከመወለድ እስከሞት ድረስ የሚቀጥል ሲሆን በነዚህ የሕይወት ጉዞዎች መካከል የሚገኙትን የተለያዩ ደረጃዎች ያካትታል፡፡

### 2.1.3. ሞት እና ሀዘን

የሞትን ምንነት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው መዝገበ ቃል (1993፡፡ 85) "የነፍስ ከስጋ መለየት፣ የሕይወት ፍጻሜ፣ እልፈት" በማለት ይገልጸዋል፡፡ ከዚህ ገለጻ በመነሳት አንድ ሰው ሞተ የሚባለው ነፍስ ከስጋ ሲለይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፡፡50) ደግሞ ሞት "የነፍስና የስጋ መለየት ወይም ሕይወት ማጣት" መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ሲሞት የሟች ቤተሰቦች ለተከሰተው ሞት የሚሰጡት አጸፋዊ ምላሽ በማህበረሰቡ ባህልና እምነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ስለሆነም ባህሉ የሚፈቅደው ሥነ ሥርዓት ተከናውኖ ስንብት ይደረጋል፡፡

ሞት ሁልጊዜ ያለና የሚጠበቅ ቢሆንም መቼ እንደሚሆን ግን በትክክል አይታወቅም፡፡ ሆኖም በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ሞት ከተከሰተ ሟችን ለመሸኘት አስፈላጊ የሆኑ ክዋኔዎች ተሟልተው የለቅሶ ሥነ ሥርዓት ይፈጸማል (Hill and Daniels.2008፡380)፡፡

ሞት ሲከሰት ሰዎች በጋራ ሆነው ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ሀዘን የሚገለጽበት መንገድ ደግሞ እንደየማህበረሰቡ ይለያያል፡፡ ሞት እንደተሰማ የሟች ቤተሰቦች፣ ጓደኞችና ጎረቤቶች አንድ ላይ ተሰባስበው ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ እስኪፈጸም ባሉ ሦስት/አራት ቀናት የሚኖራቸው ስሜት ፍጹም በሀዘን የተሞላ ነው "ሀዘናቸውን ለመግለጽ ይተክዛሉ፣ ዋይ ዋይ በማለት ደረታቸውን

ይደቃሉ፣ ጸጉራቸውን ይላጫሉ ወይም ያሳድጋሉ፡፡ እንዲሁም ሀዘንተኛ መሆናቸውን የሚገልጽ የተለያየ አለባበስ ይለብሳሉ" (Cohen.1980፡3)፡፡

በሀዘን ሥነ ሥርዓት ላይ የሚታየው ሁኔታ ማህበረሰቡ በሰጠው ማህበራዊ ደረጃ መሠረት የሚወሰን ነው፡፡ ሟች በሕይወት ሳለ የነበረው ማንነት እና ደረጃ ማለትም ሀብታም፣ ደሃ ወይም ጀግና መሆን እንዲሁም በአካባቢው የሰራው ሥራ የሀዘኑን ሁኔታ የተለያየ እንዲሆን ያደርጋል (Brown. 1963፡49)፡፡

ከላይ እንዳየነው የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔም እንደ ሟቹ እድሜ፣ ፆታና ማህበራዊ ደረጃ የተለያየ ነው፡፡ ሟች መሞቱ ከተሰማበት ከመጀመሪያው እለት ጀምሮ እስከሀዘኑ ማብቂያ ድረስ የሟች ቤተሰቦችና ጓደኞች ሀዘናቸውን የሚገልፁበትም የራሳቸው የሆነ መንገድ አላቸው፡፡

### 2.2. የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ

የዚህ ጥናት የንድፈ ሀሳብ መሰረቶች ክዋኔያዊ እና ዐውዳዊ ንድፈ ሀሳቦች ናቸው፡፡ በንድፈ ሀሳቦቹም ከዕለተ ሞት እስከሀዘን ማብቂያ ያሉ መዋቅራዊ ሂደቶች ተተንትነው ተተርጉመዋል፡፡

#### 2.2.1. ክዋኔያዊ ንድፈ ሀሳብ

ክዋኔ በዋናነት እንደተግባቦት ባህርይ እና አይነት የሚወሰድ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የሚፈጸሙ ኪናዊ ጉዳዮችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ክዋኔ በራሱ መንገድ ተቀምሮ ለታዳሚ የሚደርስና የሚከወን ጉዳይ ሲሆን ሰዎች በተግባቦት ሂደት ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው (Bauman.1992፡3)፡፡

ክዋኔ አንድ ማህበረሰብ ባህሉን በድርጊት የሚገልጽበት መንገድ በመሆኑ የአንድን ማህበረሰብ ክዋኔ በተገቢ ሁኔታ በማጥናት በፊት የነበረውንና አሁን ያለውን የከዋኙን የመከወን ብቃት፣ የታዳሚውን የአተረጓጎም ሂደትና የተከሰቱ ለውጦችን በመመርመር አስተሳሰባቸውን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ክዋኔ የሁሉም የፎክሎር ዘውጎች መገለጫ ባህርይ ነው "All expression of folklore are performances, nonetheless" (Sims and Stephens, 2005:12)፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት ሥነ ሥርዓት እንደመሆኑ ሥነ ሥርዓት ካልተከወነ ህልውና ሊኖረው አይችልም፡፡ ክዋኔው የሚተላለፍበት ዘዴ ደግሞ የመልዕክቱ አንድ አካል ሆኖ መልዕክቱን መግለጽ በሥነ ሥርዓቱ የተካተተ ነው "If there is no performance there is no ritual; performance it self is an aspect of that which is performed. The medium is part of the message more precisely it is the meta message about what ever is encoded in the ritual" (Rapaport. 1992፡250)፡፡

ለክዋኔ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ከሚባሉ ነጥቦች መካከል ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ዐውድና የክዋኔ ጠቋሚዎች ይጠቀሳሉ (Sims and Stephens. 2005:134)፡፡ እነዚህን መሰረታዊ ጉዳዮች ከሀዘን ሥነ ሥርዓት አንጻር ስንመለከት ከዋኝ በሀዘን ሥነ ሥርዓት ላይ ሟችን እያሞጋገሰ ሌሎች ሰዎች ሀዘናቸውን እንዲገልጹ ሲያደርግ

ታዳሚ ደግሞ ሙሾ በመቀበልና በማልቀስ ይሳተፋል፡፡ ዐውድ ደግሞ አንድ ክዋኔ ሲከወን ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ይመለከታል፡፡ ይህም ክዋኔው የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ፣ በከዋኝና በታዳሚ መካከል ያለውን መስተጋብር እንዲሁም የመከወኛ ቁሳቁሶች ጭምር ያጠቃልላል፡፡ የክዋኔ ጠቋሚዎች በከዋኝና በታዳሚ መካከል ያለ መስተጋብር እንዲሰምር የሚያደርጉ የክዋኔውን ሥርዓት መልክ የሚያሲዙ፣ የከዋኝና የታዳሚን የክዋኔ ቅደም ተከተል የሚያሳውቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ሲጠና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲሁም የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ሲተነተን ከክዋኔው ጀርባ ያለው የማህበረሰብ አመለካከትና ስሜትም በወጉ ሊፈተሽ ይገባል፡፡

### 2.2.2.. ዐውዳዊ ንድፈ ሀሳብ

ዐውድ በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ወቅት ያለዉን አጠቃላይ ሁነት ማለትም በክዋኔው ወቅት የሚከሰቱ ጥቃቅን ክስተቶችን ሳይቀር የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው፡፡ Ben-Amos (1993፡210) የአንድ ፎክሎር ክዋኔ ሁለንተናዊ ሂደት ትርጉም የሚኖረዉ በዐውዱ እና ዐውዱ በሚሰጠዉ ትርጉም መሰረት ሲጠና መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም በሀድያ ብሔረሰብ ባህል ከእለተ ሞት አንስቶ እስከሀዘን ማብቂያ ባሉ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ በመገኘት የተሰበሰቡ መረጃዎች በተገኙበት ዐውድ መሠረት ተተንትነዋል፡፡

የዐውድ አይነቶችን ምሁራን በተለያየ መንገድ ይመድባሉ፡፡ ከነዚህ መካከል Sims and Stephens (2005፡138) ዐውድን “ተጨባጭ” ዐውድና “ማህበራዊ” ዐውድ ይሉታል፡፡ ተጨባጭ ዐውድ የሚባለው አንድ የፎክሎር ቅንጣት የሚከወንበትን ተረጋጋጭ ነገርና የሚታይ አካባቢ የሚመለከት ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ተጨባጭ ነገሮች የምንላቸው ከዋኙ የሚያሳየውን የፊት፣ የዓይን፣ የእጅ እንቅስቃሴ፣ የድምጽ አወጣጥ ውፍረትና ቅጥነት፣ የአድማጩን ስሜት እንዲሁም በከዋኝና በታዳሚ መካከል ያለን ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ተጨባጭ አካባቢ የሚባለው ደግሞ የፎክሎር ክዋኔ የሚቀርብበትን ቦታና ጊዜ እንዲሁም በክዋኔው ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችን ይመለከታል፡፡ ሁለተኛው የዐውድ ዓይነት ማህበራዊ ዐውድ ነው፡፡ ይህ ዐውድ በፎክሎር ክዋኔ ወቅት የክዋኔውን ባለቤት ሁኔታ፣ ባህል፣ ዕድሜ፣ ፆታ ባጠቃላይ በከዋኝና ታዳሚ መካከል ያለውን መስተጋብር ይመለከታል፡፡

Bauman ደግሞ ዐውድን “ማህበራዊ” እና “ባህላዊ” በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ ባህላዊ ዐውድ በውስጡ ልማዳዊ ተግባራትን እና የሰዎች አኗኗር በፎክሎሩ ውስጥ የተቀረጸበትን መንገድ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ ሀይማኖት፣ ዝምድና፣ ጉርብትና፣ ከበራ፣ ጸሎት ያሉ ማህበራዊ እሴቶችን ይመለከታል፡፡ ማህበራዊ ዐውድ ደግሞ ማህበራዊ መዋቅሮችንና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በውስጡ ይይዛል፡፡ እንዲሁም በከዋኙና በታዳሚው መካከል የሚኖረውን መስተጋብር ያጠቃልላል (1983፡363)፡፡

የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥብ የሚመሠረተው Bauman ባስቀመጧቸው ባህላዊ ዐውድና ማህበራዊ ዐውድ በሚለው ነው፡፡ ምክንያቱም በባህላዊ ዐውድ ስር ሰፊ የሆነውን የማህበረሰብ አስተሳሰብ እና ልማዳዊ ህግጋት እንዲሁም ሌሎቹን የዐውድ ዓይነቶች መመልከት ይቻላል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በሀድያ ብሔረሰብ ባህል ላይ የተጠኑ በርካታ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆነው በአየለ መሎሬ በ (1986) ዓ/ም "የሀድያ ህብረተሰብ  የለቅሶ ሥርዓት" በሚል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የተጠናው ጥናት ነው፡፡ በጥናቱ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከናወነውን ለቅሶ ከልደት እስከ ሙሽርና ለደረሱና ለአዛውንት ብሎ በመክፈል ቅድመ ቀብርና ቀብር ላይ ያለውን ሥርዓት አሳይቷል፡፡ ነገር ግን መረጃውን የሰበሰበበትን ዘዴ በግልጽ አላሰፈረም፡፡ የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በተፈጥሮአዊ መቼቶች መሆናቸው የተለየ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ከሚነሱ ነጥቦች ስፋትና ትኩረት አንጻር ልዩነቶች ይኖራሉ፡፡

የሀድያን ብሔረሰብ ባህል በማስተዋወቅ የሚጠቀሰው መጽሐፍ[8] "የሀድያ ህዝብ ታሪክና ባህል" በአለባቸው ኬዕሚሶ እና ሳሙኤል ሀንዳሞ (2002) የተጻፈው ሲሆን ይህ መጽሐፍ የሀድያን ባህል ለሌሎች በማሳወቅ ረገድ የሚጠቀስ አብዛኛውን የባህሉን ገጽታ በስፋት የዳሰሰ ሥራ ነው፡፡ መጽሐፉ በውስጡ የሕዝቡን አኗኗር፣ ቋንቋ፣ የህዝቡን ታሪካዊ ጉዞ፣ የሀድያን ሴራ ከነመዋቅሩ፣ የሀድያን ጥንታዊ ሀይማኖት በመጨረሻም በሀድያ ከልደት እስከሞት ያሉ ወጎችን ይዳስሳል፡፡ በመጽሐፉ ከልደት እስከሞት በተገለጸው ክፍል የሀዘን ሥነ ሥርዓቱን ለማሳየት መሞከሩ ከዚህ ጥናት ጋር ቢያመሳስለውም ይህ ጥናት የሀዘን ሥነ ሥርዓት መረጃዎችን ከተፈጥሮአዊ ዐውድ በምልከታ በመሰብሰብ በንድፈ ሀሳብ መሠረትነት መተንተኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡

## 3. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በተጠኚዎቹ ባህል ውስጥ ተገኝቶ ከባህሉ ባለቤቶች የሀዘን ሥርዓተ ክዋኔ መረጃዎች ለማጥናት ያለመ በመሆኑና መረጃዎችን ከመስክ በመሰብሰብ የመረጃ ፍቺዎችን በትንተና የማውጣት አካሄድ ስላለው አይነታዊ ምርምር ሊባል ይችላል፡፡

የጥናቱን አላማዎች ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችል ዘንድ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች ዓላማ ተኮር ንሞናን በመጠቀም በተመረጡ አራት ወረዳዎች ከተከሰቱ የሀዘን ሥነ

[8] Braukamper (2014) Fandaanano: The Traditional Socio-Religious System of the Hadiyya  in Sothern Ethiopia. እና Braukamper and Tilahun Mishago (1999) Praise and Teasting: Narrative songs of the Hadiyya in Southern Ethiopia.በሀድያ ብሔረሰብ ላይ ትኩረት አድርገው የተጻፉ ሌሎች ተጠቃሽ ሥራዎች ናቸው፡፡

ሥርዓቶች በአራት ተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ (በሁለት የእድሜ ባለጸጋና በሁለት ወጣትና ጎልማሳ) በመገኘት የተሰበሰቡ መረጃዎች ሲሆኑ ካልአይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ስለአካባቢው የተጻፉ የተለያዩ ሰነዶችን በመፈተሽ የተገኙ ናቸው።

መረጃዎች ከመስክ የተሰበሰቡት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴ ነው። በመስክ ቆይታ ወቅት ካጋጠሙ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች በአራቱ ላይ በመገኘት በተሳታፊ ምልከታ የነበረውን አጠቃላይ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል።

ቃለ መጠይቅ አንድ አጥኚ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የሚፈልገውን መረጃ ሊሰጡኝ ይችላሉ ብሎ ካመነባቸው ግለሰቦች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ በመጠየቅና በመመለስ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው (Goldstein.1964፡104)::

ጥናቱን ለማከናወን ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ወሳኝ የሆኑ መረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥ የዓላማ ተኮር ንሞና (purposeful sampling) ዘዴ እና ጠቋሚ ወይም ተያያዥ ንሞና (Network or Snowball sampling) ጥቅም ላይ ውለዋል። ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ "ተመራማሪው ተሳታፊዎችን የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንጻር እነማንን ብመርጥ የምፈልገው መረጃ ኗሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የትኞቹንስ ባሳትፍ የጥናቱ ዓላማ ይሳካል?" በማለት የመምረጫ ዘዴ ሲሆን ጠቋሚ ወይም ተያያዥ የንሞና ዘዴ "አንዱ ሌላውን በመጠቆም ወይም ተመራማሪው በፊት ያገኘው የኋለኛውን እያመለከተ በመጓዝ" መሆኑን ያስረዳሉ (ያለው።2009፣136-137)።

በመሆኑም በዚህ ጥናት ለቃለ መጠይቅ የተመረጡ የመረጃ ሰጪዎች ስለብሔረሰቡና ስለባህሉ በሚገባ የሚያውቁ የሀገር ሽማግሌዎች እና ስለሀዘን ሥነ ሥርዓቱ መረጃ መስጠት ይችላሉ ተብለው በአካባቢው ነዋሪዎች የተጠቆሙ ናቸው። በዚህ መሠረት አስራ አምስት ሰዎች በቃለ መጠይቅ መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል። ከነዚህ መካከል 12ቱ ወንዶች ሲሆኑ 3ቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በሀድይኛ ቋንቋ ሲሆን ለሥራው ያመች ዘንድ ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል። ለትርጎማው የተመረጡ ሁለት ሰዎች[9] ከዚህ ቀደም በሀድይኛ ቋንቋ የተዘጋጁ መጽሐፍትን ወደአማርኛ በመተርጎም የሚታወቁ ሲሆኑ የሀድይኛውን ፍቺ ቃል በቃልና ዐውዳዊ ትርጉሙን ተርጉመዋል።

## 4. የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ዐውዳዊ ትንተና

በዚህ ክፍል የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ሂደት ከተለያዩ ገጽታዎች አንጻር ተተንትኖ ቀርቧል። የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በሀድያ ብሔረሰብ የሚከወነውን የሀዘን ሥነ ሥርዓት በሁለት ክፍሎች መመደብ ይቻላል። እነዚህም የዘወትር/የተራ ሰው እና የታዋቂ ሰው የሀዘን ሥነ ሥርዓት ናቸው።

[9]አቶ መንገሻ ጎቤቦ እና አቶ ማርቆስ ሞላ።

## 4.1. የዘወትር/የተራ ሰው የሀዘን ሥነ ሥርዓት

በሀድያ ብሔረሰብ መኖሪያ አካባቢ አንድ ሰው መሞቱ እንደተሰማ የሟቹ የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶች ተሰባስበው ስለ ለቅሶው ሁኔታ ይመካከራሉ፡፡ በምክክራቸውም “ሟች እድሜው ምን ያህል ነው? ማህበራዊ ደረጃውስ እንዴት ነው? የሀገር አስተዳዳሪ ነበር ወይስ አስታራቂ? ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ቀረቤታ ምን ያህል ነው? ምን ምን ሥራዎችን ሰርቷል?”[10] የሚሉ ጉዳዮች ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡ እነዚህ ነጥቦች የሀዘን ሥነ ሥርዓት አከዋወን ሂደቱን የተለያየ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም የዘወትር ሞት የህጻንና የወጣትና የጎልማሳ ሞት በሚል ይፈረጃል፡፡

### 4.1.1. ህጻን[11] ሲሞት የሚከናወን የሀዘን ሥነ ሥርዓት

በሀድያ አካባቢ ሰው ሲሞት የሀዘኑ ልክ እንደሟቹ እድሜና የአሟሟት ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ በመሆኑም እድሜው ከስድስት ወር በታች የሆነ ህጻን ከሞተ/ች ለቅሶ አይለቀስም፡፡ ሀዘኑ የሚበረታው እናት ላይ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ እምነት “እናት አዛኝ በመሆኗና ዘጠኝ ወር የእርግዝና ጊዜዋን ጨርሳ ልጇን በሰላም ማቀፍ በምትጓጓበት ወቅት ላይ የልጇን ሞት መስማቷ ሀዘኗን ያበረታዋል፡፡”[12]

አንድ ህጻን በተወለደ ቀን ከሞተ ህጻኑ ሞቷል ሳይሆን ጠፍቷል (ጪሊች ቢኦኮ) ተብሎ ስለሚታሰብ ከወላጅ እናቱ በስተቀር ሌላው ሰው አያለቅስም፡፡ እሷም ብትሆን ስታለቅስ ለሌላ ሰው በማይሰማ መልኩ ድምጽ ሳታወጣ እንጂ ዜማ ባለው ለቅሶ እንድታለቅስ አይፈቀድላትም “ፈጣሪ ለራሱ የፈጠረውን ነው በጊዜ ወደራሱ የሚጠራው ተብሎ ስለሚታመን በቀጣይ የሷ የሆነውን የሚያድግ ልጅ እንዲሰጣት ከፈጣሪ ጋር መጣላት ስለሌለባት ሀዘን እንዳታበዛ ትመከራለች፡፡”[13]

ዝም ማለት አቅቷት ብትጮህ እንኳን የሰሙ ጎረቤቶች እንደምንም ለቅሶዋን በልክ እንድታደርገው ይመክሯታል፡፡ ህጻን ልጅ የሞተባትን እናት የጎረቤት ሴቶች ተሰብስበው ወንበር ላይ ቁጭ እንድትል ያደርጓትና አናቷ ላይ ቅቤ በመቀባት ሀዘኑን እንድታቆምና የሞተባት ልጅ በሌላ እንደሚተካ የተለያዩ ማጽናኛ ቃል በመንገር ያጠነክሯታል፡፡ “ቅቤ የሚቀባት እርጥብ ነገር በመሆኑ ሀዘንን ያቀዘቅዛል ብለው ስለሚያምኑ መሆኑን ወ/ሮ አዮሴ ቀዳላ ይናገራሉ፡፡”[14] እናቲቱም ሰው የሚላትን መስማት ስላለባት እንደምንም ድምጽ ሳታሰማ ለብቻዋ ታለቅሳለች፡፡

እድሜው ከአንድ አመት በታች የሆነ ህጻን ከሞተ/ች ለሩቅ ቤተሰብ ለቅሶ ድረሱ ተብሎ መልዕክተኛ አይላክም፡፡ ብዙ ሰው የተሰበሰበበት የሀዘን ሥነ ሥርዓትም አይከናወንም፡፡ እዛው ጎረቤት አካባቢ ያሉ ሰዎችና ቅርብ የሚኖሩ ቤተዘመዶች ብቻ ሆነው ወዲያውኑ ቀብሩ እንዲፈጸም ያደርጉና ሀዘኑን በአጭሩ ያስቀራሉ፡፡

[10] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 27 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[11] በዚህ ጥናት ከ0 እስከ 1 ዓመት እድሜ ያላቸውን የሚመለከት ነው፡፡
[12] ወ/ሮ መስቀሌ ፍራንሴ፣ ቃለ መጠይቅ (ታህሳስ 2 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[13] አቶ ጴጥሮስ አንሼቦ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥር 6 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[14] ቃለ መጠይቅ (ህዳር 13 ቀን 2012 ዓም)፡፡

ምክንያቱም ሌላ ልጅ እንዳይወለድና ጥሩ እድል እንዳይመጣ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በአካባቢው ሞት ያበዛል ተብሎ ስለሚታመን እንደተቀበረ ወዲያው ሀዘኑ እንዲቆም ይፈለጋል "ህጻን የሞተባቸው ወላጆች ከቀብር በኋላ የሰማ ሰው እንዳይመጣና ሀዘኑ እንዳይቀጥል ለማድረግ ቤት ውስጥ አይቀመጡም፡፡ እናት ወደገበያ አባትም ወደ እርሻውና ወደሚሰራው ሥራ ይሰማራሉ፡፡"[15]

ህጻኑ አንድ አመት የሞላው ወይም ለአመት የተቃረበ ከሆነ ግን የሰፈር ሰውና የእድር አባላት ተሰብስበው የሀዘን ሥነ ሥርዓቱን ይፈጽማሉ፡፡ ነገር ግን ሀዘኑ ከአንድ ቀን አያልፍም "ህጻናት ለአለሙ አዲስ በመሆናቸውና ሰው ስለማያውቃቸው ሀዘን መብዛት የለበትም፡፡ ሀዘን በዝቶ ሌላ ሀዘን እንዳይፈጠር ቅርብ ያሉ ሰዎች ብቻ ተሰብስበው ወዲያው ይቀብራል፤ሀዘኑም ቶሎ ይቆማል፡፡"[16]

በሀድያ አካባቢ እስከአንድ አመት ያሉ ህጻናት ሲሞቱ እንደአዋቂ አይገነዙም፡፡ አቶ ዮሐንስ ሀንቄቦ እንደሚሉት "ህጻናት ምንም ስለማያውቁ በጨርቅ ይጠቀለላሉ እንጂ አይገነዙም፡፡"[17] የቀብር ሥነ ሥርዓቱ አፈጻጸምም እንደእድሜያቸው ይለያያል፡፡ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ያሉ ህጻናት ሲሞቱ በጨርቅ ተጠቅልለው በትልቅ እንስራ ስባሪ ውስጥ ይደረጉና ከመኖሪያ ቤቱ ጓሮ ይቀበራሉ፡፡ መቃብሩ ምልክት እንዳይኖረውም ቦታው ላይ እንሰት ይተከላል፡፡[18] እንሰት የሚተከለው ቦታው የመቃብር መሆኑ እንዲረሳና በእንሰቱ ብቻ እንዲታወስ ለማድረግ ነው፡፡ ለቅሶ የሰሙ ጎረቤቶች ማጽናኛ ምርቃት የሚሰጡት "እግዚአብሔር በልጅ ይክፈላችሁ"[19] በማለት ነው፡፡ በማህበረሰቡ አመለካከት ህጻን ከሞተ በሌላ ህጻን እንደሚተካ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ህጻን የሞተባቸው ወላጆች በምትኩ ሌላ ልጅ ፈጣሪ እንዲሰጣቸው ይጸለይላቸዋል፡፡

### 4.1.2.. ወጣትና ጎልማሳ ሲሞት የሚከናወን የሀዘን ሥነ ሥርዓት

በሀድያ ባህል መሰረት ለወጣትና ለጎልማሳ የሚከወን የሀዘን ሥነ ሥርዓት ወጣት ሆነው ትዳር ለመሰረቱና ለወለዱ እንዲሁም ለአቅመ አዳምና ሄዋን ደርሰው ሳያገቡና ሳይወልዱ ለሚሞቱ በአብዛኛው ከ18-60 አመት ላሉ ሰዎች የሚደረግ የሀዘን ሥነ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡

በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ ለሞተ ሰው የሚደረገው የሀዘን ሥነ ሥርዓት በመሪር ሀዘን የተሞላ በመሆኑ በደንብ ይለቀሳል፡፡ በተለይ እድሜያቸው ለአቅመ አዳምና ሄዋን ደርሶ ሳያገቡና ሳይወልዱ ለሞቱ የብሔረሰቡ አባላት በከፍተኛ ሁኔታ ይታዘናል፡፡ ምክንያቱም እራሳቸውን ችለው ቤተሰብን በማስተዳደሪያ እድሜ ላይ በማለፋቸውና ዘራቸውን ሳይተኩ በመሞታቸው ቤተሰቡን ብቻም ሳይሆን በመንደሩ ያለን ሰው ሁሉ መሪር ሀዘን ውስጥ ይከታሉ፡፡ የወለዱ ሲሆኑ ካልወለዱት አንጻር

[15] አቶ ወልዴ አሼቦና አቶ ዘኪዎስ ሰጋሮ፣ ቃለ መጠይቅ (ህዳር 13 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[16] አቶ መንገሻ ገበየሁ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 12 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[17] ቃለ መጠይቅ (ታህሳስ 8 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[18] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 08 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[19] አቶ ኮያሞ መኤዶ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 6 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

ሲታይ ዘራቸውን አስቀጥለው በመሞታቸው በተወሰነ መልኩ የመጽናናት ስሜት ቢኖርም የወለዷቸውን ልጆች በሚገባ ሳያሳድጉ፣ ለወግ ማዕረግ ሳያበቁና ሕይወትን በሚገባ ሳይኖሩ በማለፋቸው በህዝቡ ዘንድ የሚፈጠረው የሀዘን ስሜት ቀላል አይደለም፡፡

ከሌላው በተለየ እናት ላይ የሚደርሰው ሀዘንና መጎዳት ግን ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም አባት ቆሞ ከማልቀስ በተጨማሪ ለመስተንግዶ የሚሆኑ ነገሮችን ለማሟላትና የቀብር ቦታን ለማመቻቸት ወጣ ገባ ስለሚል በተወሰነ መልኩ ፋታ ያገኛል፡፡ እናት ግን ከአባት ይልቅ አርግዛ ወልዳ ተቸግራ አሳድጋ ልጇን በማጣቷ እስኪቀበር ከአስከሬኑ አጠገብ ዞር ስለማትል ሀዘኗ የከፋ ይሆናል፡፡[20]

ሟቹ  ትዳር ያልመሰረተ ከሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚፈጥረው ድንጋጤ ከፍተኛ በመሆኑ በከባድ ለቅሶ ይታጀባል፡፡ ቤተሰቦቹና ለቅሶ ደራሾችም ወይኔ ወንድሜ (አዬ እያባዮ) እያሉ ያለቅሳሉ፡፡ ሴት ከሆነች የኔ ወጣት (ኢ ባጆ)፣ እህቴ (እያይቼ) እያሉ ያለቅሱላታል፡፡ አግብተው ልጅ የወለዱ ከሆነ "ወንዱን ሴቱን ወልደዋልና ልጆቻቸውን እዩ፣ በልጆቻቸው ተጽናኑ፣ አታልቅሱ"[21] እየተባለ ሀዘኑን ለማስቆም ቢሞከርም ሦስት አራት ቀን ቀብሩ እስኪፈጸም ቤተሰቡ ምርር ያለ ለቅሶ ማልቀሱ የማይቀር ነው፡፡

### 4.2. የታዋቂ ሰው የሀዘን ሥነ ሥርዓት

የታዋቂ ሰው ሞት በጦርነት፣ በልማት፣ በበጎነት፣ በአስታራቂነት በመሳሰሉት በአርዓያነት የሚጠቀሱ ጀግኖች፣ የጀግና ሚስቶች እና የእድሜ ባለፀጎች ሞትን የሚመለከት ሲሆን በባህሉ የተደነገጉ ልዩ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች የሚፈጸምላቸው ናቸው፡፡

#### 4.2.1. ጀግና ሲሞት የሚከናወን የሀዘን ሥነ ሥርዓት

ለጥናቱ በተመረጡ ወረዳዎች ቀደም ሲል በነበረው ልማድ መሠረት  አንድ ሰው ጀግና የሚባለው  በጦርነት ወቅት ዘምቶ የማረከ ወይም በአደን የተለያዩ የዱር እንስሳትን በመግደል የሚታወቅ ሲሆን ነበር፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ በማህበረሰቡ ዘንድ ጀግና የሚባሉት በአካባቢው የተለያየ ሹመትና የማዕረግ ስም የተሰጣቸው፣ በአስታራቂነት፣ በልማትና በበጎነት የሚታወቁ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ሲሞቱ በሕይወት ዘመናቸው የሰሩት ሥራ ሳይነገርላቸው ዝም ተብሎ እንደሌላው የማህበረሰብ አባል አይቀበሩም፡፡[22]

በመንደሩ የሚታወቅ አስለቃሽ[23] ተመርጦ አስለቃሹ "ሞራ" እያለ ሲያስለቅስ ተቀባዮቹ ደግሞ "ሆሞራ" እያሉ ይቀበሉታል፡፡ ሞራ ማለት ኀበዝና ጀግና ማለት ሲሆን የሚያውቀው ሰው ሁሉ ሟች በሕይወት ዘመኑ የሰራውን ጀግንነት በዜማ

[20] አቶ ኮያሞ መኤዶ፣ ቃለ መጠይቅ (ህዳር 14 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

[21] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

[22] አሁን ባለው የለቅሶ ሥነ ሥርዓት ገበያ ባለበት ቦታ እየዞሩ ስለሟች መናገር ቢቀርም ሌላው ሥርዓት ግን አሁንም ይከወናል፡፡

[23] ገንዘብ ተከፍሎት ስለሟች ጀግንነት እየተናገረ የሚያስለቅስ የሟች ቤተሰብ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

እየተናገረ ያለቅስለታል "ስለሟች የሚወራው ጀግንነት በሕይወት ያሉትን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሱ ለመሆን እንዲሞክሩ ያነቃቃቸዋል፡፡"[24]

ጀግና ወይ ጦረኛ የሆነ ሰው ሲሞት ገድሉንና ክብሩን የሚያመለክቱ ሥርዓቶች ይከናወናሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ፈረስ፣ ጦር፣ ጋሻ፣ ጎራዴ፣ የነብር ቆዳ፣ የአንበሳ ቆዳ፣ ደማቅ የሆነ ቀሚስ የለበሱ የሚጎተቱ ፈረሶች እንዲሁም ፈረሶችን የሚጎትቱ ሰዎች ይመረጣሉ "እነዚህ ዕቃዎች ሟች በሕይወት በነበረበት ጊዜ የተለያዩ የዱር እንስሳትን መግደሉንና ጀግና መሆኑን ማሳያ ናቸው፡፡" [25] እንዲሁም ለዘመድ አዝማድ "በዚህ ቀን የኤከሌ ለቅሶ ነውና ድረሱ" እየተባለ መልዕክተኛ ይላካል፡፡

በቀብሩ ዕለት ጥሩ የሚባል አቀንቃኝ ብር ተከፍሎት እንዲመጣ ይደረግና ስለሟች እየፎከረ እንዲያስለቅስ ይደረጋል፡፡ የሟቹን ስም እየጠራ ሞተ/ኮበለለ (ዶዩኮ)፣ ጀግና (ሞራ)፣ማንም አይስተካከልህም (አይም ኪኒ ጉዶዮ) እያለ እየተንጎራደደ ያስለቅሳል፡፡ ለቀብሩ የመጡ ሰዎችም ሰብሰብ እያሉ  እያሉ ሟች የተወለደበትን ቦታ፣ የማን ጎሳ እንደሆነ፣ የሰራውን ሥራ በዜማና በግጥም እየተናገሩ ሀዘናቸውን ይገልጻሉ::

የቀብር ሥነ ሥርዓት ከመከናወኑ በፊት የሟቹን ማንነት የሚያወሱ አራት ሀዘን ነጋሪዎችና ጎበዝ ፈረስ ጋላቢዎች ጥሩ አቋም ካላቸው ፈረሶች ጋር ተመርጠው ገበያ ባለበትና ብዙ ሰው በሚሰበሰብበት ቦታ ሁሉ እየቆሙ ስለሞተው ሰው ማንነትና ቀብሩ ስንት ሰአት እንደሆነ እንዲናገሩ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሀዘን ነጋሪዎች አረዳኖ/አረጃኖ[26] ሲባሉ የማወጁ ሂደት ደግሞ አረዲማ[27] ይባላል፡፡ አዋጁ በሚነገርበት ጊዜ ለቅሶውን የሰማና የድግሱን ሁኔታ የተረዳ ሰው ሟቹን ባያውቀው እንኳን የሚከናወነውን የሀዘን ሥነ ሥርዓት ለመመልከት በቀብሩ ዕለት ወደቦታው ስለሚሄድ የለቅሶው ድባብ ይደምቃል፡፡

ሀዘን ነጋሪዎቹ ወደ ተልዕኳቸው ከመሰማራታቸው በፊት ማታ ላይ የሚበላና የሚጠጣ ቀርቦላቸው ከበሉና ከጠጡ በኋላ ገበያ ወጥተው የሚናገሩትን ግጥም በዜማ  ለተሰበሰበው ሰው እንዲናገሩ ይደረጋል፡፡ የሟቹን ጀግንነት፣ በሕይወት ሳለ ምን ምን ነገሮችን እንደሰራ፣ የማን ቤተሰብ እንደሆነ እየተናገሩ በየመሀሉ የሟችን ስም እየጠሩ ሞተ (ዶያኮ) እያሉ ሲለፍፉ ያድራሉ፡፡ ይህም የአፍ ፍተሻ (ሱም ሞኢማ) [28] ይባላል፡፡ "በዚህ ልምምድ ወቅት በቤተሰቡ ተገምግሞ እንደሚፈለገው ያልተናገረ ሀዘን ነጋሪ ይቀርና በትክክል ስለሟች ጀግንነት ያወሩ ብቻ ተመርጠው ሌሊቱን ሲለማመዱ ያድራሉ፡፡"[29]

ጀግና ሰው በጸና ከታመመ በአካባቢው የሚኖሩ አፈ ታሪክ ተናጋሪዎችን (ጉንቴ ያዶራሞ) ሰብስቦ "ከሞትኩ በኋላ ጀግና እንደነበርኩ፣ አሸንፌ መኖሬን፣ ሀብታምና

---

[24] አቶ ዘኪዎስ ሰጋሮ፣ ቃለ መጠይቅ (ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[25] አቶ መንገሻ ጎቤቦ፣ ቃለ መጠይቅ (ታህሳስ 29 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[26] ሀዘን ነጋሪ የሚባሉት ገበያ ባለበትና ሰው በተሰበሰበበት ስለሟች ዝና የሚያወሩና ላልሰማ የሚያሰሙ ናቸው፡፡
[27] የሀዘን ጥሪ፡፡
[28] ወደተሰማራበት ቦታ ሲሄድ ስለሟች ምን ምን እንደሚል አስቀድሞ በቤተሰብ  ፊት ይለማመዳል፡፡
[29] አቶ መንገሻ ገበየሁ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 3 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

ብዙ መሬት እንዳለኝ ታሪኬን ለማያውቁ ንገሩልኝ[30] በማለት አስቀድሞ የሕይወት ታሪኩን ይነግራቸዋል፡፡ የመናገር እድሉን ሳያገኝ በድንገት ከሞተ ደግሞ ስለጀግንነቱ በሚያውቁ ቤተሰቦቹና ጓደኞቹ አማካይነት የሠራው ሥራ እንዲነገር ይደረጋል፡፡ ስለዚህ የሟቹን የጀግንነት ታሪክ ቀድመው የሰሙ ታሪክ ነጋሪዎች የሰሙትን አንድም ሳያስቀሩ ለሀዘን ነጋሪዎቹ (ለአረዳና) ምሽት ላይ ያስጠኗቸዋል፡፡ አቶ ኮያሞ መኤዶ እንደሚሉት "ሟች በሕይወቱ የሠራው ነገር ተነግሮ መለቀሱ ወጣቱን ትውልድ እንደሱ ጠንካራ ሠራተኛ እንዲሆን ያበረታታል፡፡"[31]

ጠዋት ወደተመደቡበት አቅጣጫ ከመሄዳቸው በፊት በተዘጋጀላቸው ፈረስ ላይ ሆነው በራፍ ላይ (ነፈራ) ቤተዘመድ በተሰበሰበበት ገበያ ላይ እንዲህ እንዲህ እያልኩ እናገራለሁ (ሜራኔ ኤኢስ ኤኢስ ያ ኩሮሞ) በማለት ሞተ (ዶዩኮ)፣ የጀግና ልጅ (ሞር ቤቶ) የሟቹን ጀግንነት የት የት ተዋግቶ እንዳሸነፈ፣ ያለውን የሀብት መጠን ተራ በተራ እየተናገሩ የተሰበሰበውን ቤተዘመድ አስለቅሰው ይወጣሉ፡፡ [32] የሚመደቡት ወደተለያየ አቅጣጫ ሲሆን በተለይም ገበያ ያለበትና ብዙ ሰው የሚሰበሰብበት ቦታ ተመራጭ ይሆናል፡፡

በመንገድ ሲያልፉ የሚያያቸው ሰው በለበሱት የነብር ቆዳና ጸጉራቸው ላይ በሚሰኩት የጃርት እሾክ ያውቃቸዋል፡፡ የነብር ቆዳውና የጃርት እሾኩ ሟች የተለያዩ የዱር እንስሳት የገደለና በብሔረሰቡ እምነት ጀግና መሆኑ የተመሰከረለት ሰው እንደነበር ማሳያ ነው፡፡ በመሆኑም እነሱን ከርቀት የሚያይ ሰው የሆነ ቦታ አንድ ጀግና (ታዋቂ ሰው) እንደሞተ ስለሚገምት ማንነቱን ለማወቅ ቆሞ ስሙ እስኪነገር ታሪኩን በጉጉት ያዳምጣል "ሞትን በማወጅ ሂደት ውስጥ እሩቅ ሀገር ነዋሪ ሆኖ ሀዘኑን ያልሰማ የቤተሰብ አባል ድንገት ሲሰማ ደንግጦ እራሱን እስከመሳት የሚደርስ ሰው ሊኖር ይችላል፡፡" [33] ሀዘን ነጋሪዎች ገበያ ሲወጡ ከሚሏቸው ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

| **አማርኛ** | **ሀድይኛ** |
|---|---|
| እንዲህ አይነቱ ጀግና ሞተ | ኤሂዶ ጎንች ዶዩኮ |
| ዘጠኝ ገዳዩ ሞተ | ኡራግ ሆንስ ቤቲ ዶዩኮ |
| ሴት ልጆች ከነባሎቻችሁ | ሁለንዲ ለንድ አሮኢ |
| በተባለው ቀን ለቅሶ ድረሱ[34] | ኤ ቤላ ዊዕሎ ዋለሄ |

በአካባቢው ጀግና ሲሞት በሬ ታርዶ የሚበላና የሚጠጣ ተዘጋጅቶ በከፍተኛ ድግስ በመሆኑ ለቅሶ የሚመጣው ሰው ሟቹን ባያውቀው እንኳን ለጀግና ለቅሶ ተብሎ የሚዘጋጀው ዝግጅት ላይ ለመብላትና ለመጠጣት ይመጣል፡፡[35] የተዘጋጀው ድግስ ደማቅ እንደሆነም ሀዘን ነጋሪዎቹ ሲናገሩ ስጋ መብላት የፈለክ መቁረጫ ያዝ (ማር

[30] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[31] ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 8 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[32] አቶ ጴጥሮስ አንሼቦ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 05 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[33] አቶ ዘኪዎስ ሰጋሮ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 14 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[34] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥር 05 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[35] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 05 ቀን 212 ዓ/ም)፡፡

ሀሲቶክ ቢላው አመጤ)፣ መጠጥ መጠጣት የምትፈልግ ብርሌ ያዝ (አግ አሲቶክ ብርሌ አመጤ)[36] እያሉ ሟች ቤት የተዘጋጀው ድግስ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ተበልቶ ተጠጥቶ እንደማያልቅ ይናገራሉ፡፡

ሀዘን ነጋሪዎች የተሰጣቸውን ተልዕኮ ጨርሰው ማታ ወደ ሀዘኑ ቤት ሲመለሱ ቀን ሲናገሩ የዋሉትን ለተሰበሰበው ቤተዘመድ ማስረዳት አለባቸው፡፡ በማስረዳቱ ሂደትም የተሰበሰበውን ሰው ለአንድ ሰአት ያህል አስለቅሰው ተልዕኳቸውን በአግባቡ ስለፈጸሙ የተዘጋጀላቸውን ምግብ በልተው አረቄ ጠጥተው ገንዘባቸውን ተቀብለው ይወጣሉ፡፡

የቀብር ዕለት የሟቹ አልባሳትና የጀግንነት ዕቃዎች (ጋሻ፣ ጦር፣ ጎራዴ) ወደ ውጪ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም ለቀስተኞች ሟች ቀደም ሲል ለብሶና ይዞ ወጥቶ የሚውልበትን ዐውድ እያስታወሱ እንዲያለቅሱ ለማድረግ ነው፡፡ የሟች ሚስትም የባሏን ካፖርት ለብሳ ጀግንነቱን እያወደሰች ማልቀስና ማስለቀስ አለባት፡፡ የባሏን ካፖርት የምትለብሰው ሟች በሕይወት ሳለ አዘውትሮ የሚለብሰውና የክብር ልብሱ ካፖርት እንደመሆኑ ያን እያዩ ሰዎች እንዲያስታውሱት ለማድረግ ነው፡፡

የሟች ሚስት በሀዘን ግጥም አማካይነት ሟች ማንና የማን ቤተሰብ እንደሆነ ነግራ ማስለቀስ ከተሳናትና ዝም ብላ እንባ ብቻ የምታፈስ ከሆነ የአካባቢው ሰዎች "ከሱ እጅ አልበላሽም፣ አልጠጣሽም ለምን ዝም ትያለሽ ተናገሪ"[37] እያሉ ይወቅሷታል፡፡ የሰውን ንግግር ፍራቻ የምትችለውን ያህል ግጥም እየደረደረች ድምጿ አውጥታ ልታለቅስ ይገባል፡፡ ከቀብር በኋላም "ጸጉሯን ትላጫለች፣ ጥፍሯን አትቆርጥም፣ ጥቁር ልብስ ለብሳ ሀዘን ላይ መሆኗን ትገልጻለች፡፡"[38]

### 4.2.2.. የጀግና ሚስት ስትሞት የሚከናወን የሀዘን ሥነ ሥርዓት

በሀድያ ብሔረሰብ የጀግና ሚስት ስትሞት ባሏ ያለበትን ደረጃ ትይዝና በደማቅ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ትሸኛለች፡፡ በተለይ ባሏ በሕይወት እያለ እሷ ቀድማ ከሞተች ከፍተኛ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ይከናወንላታል፡፡ ምክንያቱም ባሏ ጀግና በመሆኑ ምክንያት በማህበረሰቡ ዘንድ ስለሚታወቅና ስለሚከበር እሱን የሚያውቅ ሰው ሁሉ በቀብሯ እለት ስለሚገኝ ለቅሶዋ ደማቅ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከላይ ለጀግና ወንድ እንደተደረገው ወሬ ነጋሪዎች ገበያ ባለበት እየዞሩ ስለጀግንነቷ አይተርኩላትም፡፡

ሟች በአካባቢው በባሏ ዝና ከመታወቋ ውጪ በሕይወት በነበረችበት ጊዜ የነበራት የእንግዳ አቀባበል፣ መስተንግዶዋ፣ የቤት አያያዟ፣ ለቅሶ ሲኖር መድረስ አለመድረሷ ከግምት ውስጥ ይገባና የተመሰከረላት ከሆነች የለቅሶዋ ዓይነትና ደረጃ ይጨምራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሴቷ ማህበራዊ ኑሮ ማለትም የታመመን በመጠየቅ፣ የሞተን በመቅበር፣ በሠርግ ሥነ ሥርዓት በመሳተፍ ከወንዱ የተለየ ከሆነ የሴቷ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ከባሏ የሚደምቅበት ጊዜ አለ፡፡

[36] አቶ ዮሀንስ ሀንቂቦ፣ ቃለ መጠይቅ (የካቲት 05 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[37] ወ/ሮ ሊንቶ አባጎ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥር 17 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[38] ጴጥሮስ አንሼቦ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥር 06 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

መረጃ ሰጪዬ አቶ መንገሻ ጎቤቦ[39] እናትና አባታቸው ሲሞቱ የነበረውን የሀዘን ሥነ ሥርዓት ሁኔታ አነጻጽረው ሲናገሩ ወላጅ አባታቸው የወንጌል ሰባኪ ስለነበሩ ለራሳቸው ጉዳይ ወደዚህ ወደዚያ ከማለት በስተቀር ሰው ሲሞት ብዙም አይሄዱም። እንደውም ለቅሶ ማሞቅ (ዊል እቢሻ) አያስፈልግም፤ አስሬ ቢለቀስ የሞተ አይመለስም፤ አታልቅሱ የሚሉ ነበሩ። እናታቸው ደግሞ በሰፈሩ በደግነታቸው የታወቁ፣ የታመመን ጠያቂ፣ የሞተን ቀባሪ እንደሆኑ የተመሰከረላቸው ነበሩ። እናታቸው ከአባት ቀድመው ነበርና የሞቱት ለቅሶአቸው በጣም ከባድና በብዙ ሰው የታጀበ ነበር። በሦስተኛው አመት አባት ሲሞቱ ግን የነበረው የሀዘን ሥነ ሥርዓት በብዙ ሰው የታጀበ አልነበረም።[40]

በመሆኑም ሴቷ ከወንዱ በተሻለ በማህበራዊ ኑሮ ተሳትፎ ካላት ከባሏ በበለጠ ሁኔታ ለቅሶዋ ይደምቃል። ስለዚህ በብሔረሰቡ እምነት ሟች በሕይወት በነበረ ጊዜ የነበረው ማህበራዊ ተሳትፎ የሀዘን ሥነ ሥርዓቱን ሁኔታ ይወስነዋል ማለት ነው። ይህ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ ስለሚታወቅ አብዛኛው ሰው በማህበራዊ ኑሮ በመሳተፍ ላይ ጠንካራ አቋም አለው።

### 4.2.3. የእድሜ ባለፀጋ ሲሞት የሚከናወን የሀዘን ሥነ ሥርዓት

እድሜ ባለጸጋ (ከ80 በላይ) በጸና ከታመመ በቅድመ ሞት የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት አሉ። ከነዚህ መካከል የታመመው ሰው ከመድከሙ በፊት ልጆች ካሉት ልጆቹን ሰብስቦ ማር[41] እያቀመሰ የመመረቅ ሥነ ሥርዓት እና የሕይወት ታሪክን መናገር ይጠቀሳሉ።

በጠና የታመመ ሰው አቅሙ እየተዳከመ እንደሆነ ሲረዳ ልጆቹን ሰብስቦ የመመረቅ ሥነ ሥርዓት ይፈጽማል። አንደበቱ ከመያዙ በፊት ልጆቹን ከያሉበት እንዲመጡ በማድረግ ቤተዘመድ በተሰበሰበበት ይመርቃቸዋል። ያለውን ንብረትና ያስቀመጠበትን ቦታ ይናገራል፤የሰው ንብረት/ገንዘብ እዳ ካለም ይመልሳል። እንዲሁም በአካባቢው የሚኖሩ የቅርብ ወዳጆቹን ሰብስቦ በሕይወት ዘመኑ የሰራውንና እንዲያውቁ የሚፈልገውን ታሪክ ይነግራቸዋል።[42] ምክንያቱም ትልቅ ሰው ሲሞት በሕይወት ዘመኑ የሠራው መልካም ሥራ እየተነገረ ሊለቀስለት ይገባል ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን ሟች ከመሞቱ በፊት ምንም ሳይናገር ድንገት ከሞተ ስለሟቹ ታሪክ በሚገባ ሊናገሩ የሚችሉ ሰዎች ተመርጠው የሚያውቁትን ለቤተሰቦቹ እንዲናገሩ ይደረግና በቀብሩ ዕለት ቤተሰቦቹ እየተናገሩ እንዲያለቅሱለት ይደረጋል።

እድሜው የገፋ ሰው ህመም ጸንቶበት በጣር ለብዙ ቀናት ከቆየ ዘመዶቹና ጎረቤቶቹ ተሰብስበው የሚድን ከሆነ ፈጣሪ ምህረት እንዲያደርግለትና እንዲያድነው፣ የማይድን ከሆነም ስቃዩ ሳይበዛበት በቶሎ እንዲሆን ጸሎት ይደረጋል። ይህም

---

[39] ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 6 ቀን 2012 ዓ/ም)።
[40] ቃለ መጠይቅ (ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ/ም)።
[41] በሀድያ ማህበረሰብ እምነት ምርቃት የሚሰጠው ማር በማቅመስ ነው። ማር ጣፋጭ በመሆኑ ሕይወታቸው የጣፈጠና የሰመረ እንዲሆን በማሰብ እንደሆነ የመረጃ ሰጪዎቹ ነግረውኛል። የምርቃቱ አይነት ግን እንደ ዐውዱ የተለያየ ነው (በትጭጭት ሥነ ሥርዓት፣ በሠርግና በሀዘን ሥነ ሥርዓት)።
[42] አቶ ኮያሞ መኤዶ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 30 ቀን 2012 ዓ/ም)።

በባህሉ “አይዴማ” ይባላል፡፡ [43] ጸሎታቸው ሰምሮ ነፍሱ መውጣቱ ሲረጋገጥ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ውስጥ ይቀሩና ሌሎቹን ወደ ውጪ በማስወጣት ከአስከሬኑ ጋር በተገናኝ መስተካከል ያለበትን አስተካክለው መጨረሳቸውን ውጪ ላሉ ሰዎች ያሳውቃሉ፡፡ ይህ እስከሚሆን ድረስ ማንም ሰው ድምጹን ጮክ አድርጎ ማልቀስ አይፈቀድለትም፡፡ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በጋራ በአንድ ድምጽ በመጮህ ለቅሶው ይጀመራል፡፡

የእድሜ ባለጸጋ ሲሞት የቀብር ሥነ ሥርዓቱ የሚፈጸመው በሦስተኛ ቀን ሲሆን ሦስተኛው ቀን ማክሰኞ ወይም አርብ ከሆነ አራተኛ ቀን እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው አርብ ዕለት የሳምንቱ ዋና ገበያ ማክሰኞ ሁለተኛው የገበያ ቀን እንደመሆኑ ሰዎችን ከንግዳቸው ላለማስተጓጎልና ቀብር የሚመጣው ሰው ቁጥር እንዳያንስ በማሰብ ነው፡፡ የቀብር ቀኑ ሦስት ወይም አራት ቀን የሚሆንበት ምክንያት እሩቅ ያሉ ዘመዶች እንዲሰበሰቡና ለዕለቱ መስተንግዶ የሚሆን ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖር በማሰብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሟቹ ቤተሰቦች በቀብሩ ዕለት ለሚዘጋጀው ድግስ[44] የሚሆን  አቅም ከሌላቸው በሞተ ቀን ብዙ ሰው ሳይሰበሰብ በሰፈሩ ሰዎች ብቻ እንዲቀበር ይደረጋል፡፡

የቀብሩ ዕለት ጠዋት በእድር ተረኞች አማካይነት ጉድጓድ የመቆፈር ሥራ የሚከናወን ሲሆን ከመቆፈራቸው በፊት ሟች ልጆች ካሉት የመጀመሪያ ወንድ ልጁ ቦታውን በመቆፈሪያ በመውጋት አባቱ የሚቀበርበትን ቦታ ምልክት ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ጉድጓዱን ሲወጋ የሟች ታላቅ ልጅ እንደመሆኑ ሟች አባቱን ተክቶ የቤተሰቡን ኃላፊነት ይወስዳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሀድያ ብሔረሰብ ባህል  ሴት ልጅ የመቃብር ቦታ እንድትወጋ አይደረግም፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ አግብታ ወደባሏ ቤት ስለምትሄድ አባቷን ተክታ የቤተሰቡን ኃላፊነት መረከብና የመቃብር ቦታውን መጠበቅ አትችልም ተብሎ ይታሰባል፡፡ የመቃብሩን ቦታ ወግቶ ምልክት ሲያደርግ አባቱ ካሉት ንብረቶች የሚፈልገውን አንዱን በመምረጥ የራሱ ያደርጋል፡፡[45]

የእድሜ ባለጸጋ ሞት የሀዘን ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ በላሎ ገርቤ ቀበሌ የተከናወነው የቀብር ሥነ ሥርዓት ምልከታ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡ ጥር 05/05/12 ሐሙስ ዕለት አቶ ዘውዴ ዋቺሶ የተባሉ የ90 ዓመት ሽማግሌ የቀብር ቀን ከጠዋቱ ሦስት ሰአት እስከ አስር ሰአት ለቀብር የሚመጡ ሰዎች ሁሉ እንደአመጣጣቸው አስከሬኑ አጠገብ የሟች ቤተሰብ ያሉበት ቦታ አካባቢ ለሰላሳ ደቂቃ ያህል እየተንጎራደደዱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሟች የማን ቤተሰብ እንደሆነ፣ ጎሳውን፣ በሕይወት ዘመኑ የሠራውን መልካም ሥራ እየተናገሩ ሀዘናቸውን እየገለጹ ይቀመጡ ነበር፡፡ አስር ሰአት ሲሆን የመቀበሪያ ቦታው

[43] የእድሜ ባለጸጋ ለብዙ ጊዜ በህመም ከቆየና  እንደማይድን ከታወቀ  ከስቃዩ ፈጣሪ በቶሎ እንዲገላግለው የሚደረግ የፀሎት ሥነ ሥርዓት ነው፡፡

[44] በሀድያ ባህል አንድ ሰው ሲሞት የሟች ቤተሰቦች በቂ ዝግጅት አድርገው ለቀስተኛውን  በሚገባ ማስተናገድና መሸኘት አለባቸው፡፡

[45] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (ታህሳስ 4 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

በመኖሪያ ቤቱ ፊት ለፊት ስለነበረ ወዲያው አንስተው የቀብር ሥርዓቱን ፈጸሙ፡፡ ከቀብር በኋላ የሟች የቅርብ የሆኑ ቤተሰቦች ድንኳን ውስጥ ከፊት ለፊት በተዘጋጀላቸው ቦታ ተቀምጠው የማጽናኛ ምርቃት የመቀበል ሥነ ሥርዓት ይከናወን ነበር፡፡ ይህም ምርቃት መስጠት (ሰብራት ኡዊማ) በመባል ይታወቃል፡፡

ዋዕ ሰብራት ኡዎና (ሦስት አራት ጊዜ ይደጋገማል)
እግዚአብሔር መጽናናቱን ይስጣችሁ!

እያሉ ለቅሶ ደራሽ የሆኑ ሰዎች ሲመርቁ ለቅሶ ተቀባዮቹ ደግሞ፡-

አሜን!
ጆራ አፋኮቴ
ክፉ አይድረስባችሁ

(05/05/12፣ በምልከታ የተገኘ መረጃ)

የምርቃቱ ክዋኔ ከቀብር በፊትም የሚከወን ሲሆን ከቀብር በኋላ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ምክንያቱም ከቀብር በፊት ሀዘን የሚገለጸው በለቅሶም ጭምር ስለሆነ የሚመርቀው ሰው ቁጥር ትንሽ ነው፡፡ ከቀብር በኋላ ግን ማልቀስ ስለማይፈቀድ ለቅሶ ደራሾች እየመረቁ ብቻ እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ ምርቃቱም እግዚአብሔር መጽናናትን ይስጣችሁ (ዋኢ ሰብራት ኡዎና) እየተባለ ሲሆን የሟች ቤተሰቦች "አሜን" በማለት ምላሽ ይሰጣሉ፡፡[46]

በሀድያ ማህበረሰብ እምነት በእድሜ የገፋ ሰው ሲሞት በሕይወት እያለ መስራት የሚገባውን ሠርቶ በጊዜው ነውና የሞተው ሞቱ እንደትልቅ እረፍት ይቆጠራል፡፡ አቶ ዘኪዎስ ሰጋሮ እንደሚሉት "ልጅ ወልዶ አሳድጎ የሞተ ሰው በራሱ በር ላይ እንጂ እርቆ አይቀበርም፡፡ ምክንያቱም ልጆቹ ሲወጡ ሲገቡ የአባታቸውን መቃብር እያዩ ሁሌም አብረው እንዳሉና መንፈሱ እንደሚጠብቃቸው ማሰብ አለባቸው፡፡"[47]

የቀብር ሥነ ሥርዓቱ እንዳበቃ ሽማግሌዎች ሰብሰብ በማለት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "አታልቅሱ፤ሀዘን ይብቃ" በማለት የሟቹን ቤተሰብ ለቅሶ የማስቆም ሥራ ይሰራሉ፡፡ የሟቹ ታላቅ ልጅ ወይም ወንድም በተሰበሰበው ህዝብ መሀል በመቆም "ቀብራችኋልና ቀባሪ አያሳጣችሁ (ዋሚ ታኮኮ ዋሞኮክ ሆጋኮቴ)፣ ሁላችሁም ወደቤት ሄዳችሁ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ ቀምሳችሁ ሂዱ" በማለት ህዝቡን ያሰናብታሉ፡፡ ከቀብር በኋላ ማብላትና ማጠጣት (ዎኦ አግሻ) ይባላል፡፡ ከሩቅ የመጣ የደከመ ሰው በልቶ ጠጥቶ አረፍ ብሎ ቤተሰቡን እየተሰናበተ ወደየመጣበት ይሄዳል፡፡

ከቀብር በኋላ ባሉ ሦስት አራት ቀናት ለቅሶውን ያልሰሙ ሰዎች ሲመጡ እንደ በፊቱ እንዲያለቅሱ አይደረግም "መርቃችሁ ቁጭ በሉ ሀዘን አታብዙባቸው" [48]

[46] 05/05/12፣ በአቶ ዘውዴ ዋቺሶ ቀብር ላይ በተሳትፎ ምልከታ የተገኘ መረጃ
[47] ቃለ መጠይቅ (መስከረም 18 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡
[48] አቶ ዘኪዎስ ሰጋሮ፣ ቃለ መጠይቅ (ህዳር 23 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

በማለት መርቀው እንዲቀመጡ ይነግሯቸዋል፡፡ የምርቃት ሂደቱ እስከሀዘን ማብቂያው (አንድ ዓመት) ይቀጥላል፡፡ ምክንያቱም እያለቀሱ ሀዘንን መግለጽ እንዲቆም ስለሚደረግ ሁሉም ሰው በሀዘንተኞች ፊት በመቆም እግዚአብሔር ያበርታችሁ፣ መጽናናትንም ይስጣችሁ እያሉ ይቀመጣሉ፡፡ ከቀብር በኋላ ባሉ ቀናት የመንደሩ ነዋሪዎች እየተመላለሱ የሟች ቤተሰቦችን ማጽናናት የተለመደ ሲሆን ይህም ማጽናናት (በካሪማ) በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ የማጽናናት ተግባር ከአስራ አምስት ቀን እስከአንድ ወር ሊቆይ ይችላል፡፡

ከቀብር በኋላ ሟቹ ወንድ ከሆነ አራት ቀን ሴት ከሆነች ደግሞ ከሦስት ቀን በኋላ የቤት ጠረጋ ሥነ ሥርዓት ይከናወናል፡፡ በዚህ እለት የሟቹ ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት ሌሊት 11 ሰአት ላይ ተሰባስበው እንደመጀመሪያው እለት መሪር ለቅሶ ለአንድ ሰአት ያህል አልቅሰው ይቀመጣሉ፡፡ ማልቀሱ እንዳበቃ ሽማግሌዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "ሀዘን ሲበዛ ሌላ ሀዘን ይመጣል፡፡ ስለዚህ ለቅሶ ከዛሬ ጀምሮ ይብቃ" በማለት የማጽናኛ ምርቃት ይመርቁና ለእለቱ የተዘጋጀውን ምግብ በልተው ቡና ጠጥተው ይለያያሉ፡፡

በቤት ጠረጋ እለት ለቅሶውን ቀድሞ ያልደረሰ ሰውም ሌሊት በመምጣት እርሙን ሊያወጣ ይችላል፡፡ ሟችን ለመጨረሻ ጊዜ የሚሰናበቱበት እለት በመሆኑ እንደመጀመሪያው ቀን በለቅሶ የታጀበ ነው፡፡ የሟች ሴት ልጆች እና ከሩቅ ሀገር የመጡ ቤተዘመዶች ወደየመጡበት የሚሸኙበት ከቤት ጠረጋ ሥነ ሥርዓቱ በኋላ ባሉ ቀናት በመሆኑ ቀጣዩ ሥራቸው እነሱን ወደየመጡበት መሸኘት ይሆናል፡፡[49]

የእድሜ ባለጸጋ በሞተ በዓመቱ የሀዘን ማብቂያ (ጋባ) ይዘጋጃል፡፡ በባህሉ መሰረት ሟቹ አመት ሞልቶት ሥነ ሥርዓቱ ካልተፈጸመ ነፍሱ እረፍት አታገኝም ተብሎ ስለሚታሰብ ለሟቹ ነፍሱን ማሳረፊያ ለሟች ቤተሰቦች ደግሞ የሀዘናቸው ማብቂያ እንዲሆን በማሰብ ሥነ ሥርዓቱ ይከናወናል፡፡ በዕለቱ በሬ ይታረድና ስጋው ተጠብሶ በቆጮና በቂጣ ይበላል፡፡ እንዲሁም የሚጠጣ ከማር የሚዘጋጅ መጠጥ (ዲቃሳ) ይዘጋጃል፡፡

የመብላትና የመጠጣቱ ሥነ ሥርዓት እንዳበቃ የቤተሰቡ የቅርብ የሆኑ ሽማግሌዎች ተሰባስበው ሟቹ በሕይወት ዘመኑ የነበረውን መሬት፣ ከብትና ሌሎች ቁሶች ልጆች ካሉት ለልጆቹ ልጆች ከሌሉት ደግሞ ለወንድሞቹ ያከፋፍላሉ፡፡ የውርስ ጉዳይ ከአንድ አመት በፊት ስለማይነሳ አመት እስኪሞላ መሬትና ንብረቱን ሟቹ ታላቅ ልጅ ካለው ታላቅ ልጁ፣ ሚስት ካለው ሚስቱ ወይም የሟች ወንድሞች ይቆጣጠራሉ፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረው ልማድ ንብረት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሀላፊነት የሚሰጠው ለወንዶች በመሆኑ የአባትን ንብረት የሚወርሱት ወንዶች ነበሩ፡፡ አሁን አሁን ግን ማህበረሰቡ ሴቶችንም በውርስ ማሳተፍ መጀመሩን አቶ

[49] አቶ ልቦና ጳውሎስ፣ ቃለ መጠይቅ (ጥር 07 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

ልቦና ጳውሎስ ይናገራሉ፡፡[50] በመጨረሻም በአካባቢው የሚኖሩ ሽማግሌዎች ሀዘኑ የመጨረሻ እንዲሆን የሚቹን ቤተሰብ መክረውና መርቀው ይለያያሉ፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በሀድያ ብሔረሰብ ባህል ከዕለተ ሞት አንስቶ እስከ ሀዘን ማብቂያ ባሉ መዋቅራዊ ሂደቶች የሚከወኑ ሥርዓተ ከበራዎችን በመተንተን የሀገረሰቡን ልማድ፣ እሴቶችና ማህበራዊ ግንኙነቶች መግለጽና መተንተን ላይ አተኩሮ የተሰራ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱን አላማ ለማሳካት በተመረጡ አራት ወረዳዎች ከነበሩ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ክዋኔዎች በአራት ተፈጥሮአዊ የለቅሶ መቼቶች (በሁለት የእድሜ ባለጸጋና በሁለት የወጣትና የጎልማሳ) በመገኘት በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተገኙ መረጃዎች መሰረት የሀድያ ብሔረሰብ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶችን በሁለት ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ተገልጿል፡፡ እነሱም የዘወትር/የተራ ሰው እና የታዋቂ ሰው የሀዘን ሥነ ሥርዓት ናቸው፡፡ የዘወትር ሞት የህጻን እና የወጣትና የጎልማሳ በሚል ይፈረጃል፡፡ የታዋቂ ሰው ሞት በጦርነት፣ በልማት፣ በበጎነት በመሳሰሉት በአርዓያነት የሚጠቀሱ ጀግኖች፣ የጀግና ሚስቶች እና የእድሜ ባለጸጎች ሞትን የሚመለከት ሲሆን በባህሉ የተደነገጉ ልዩ የሀዘን ሥነ ሥርዓቶች የሚፈጸምላቸው እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

በሀድያ ማህበረሰብ ዘንድ እድሜያቸው ከስድስት ወር በታች ለሆኑ ህጻናት የሀዘን ሥነ ሥርዓት አይከናወንም፡፡ በመሆኑም በሞቱ ዕለት ወዲያውኑ የሰፈር ሰው ብቻ ተሰባስቦ በመቅበር ሀዘኑ በአጭሩ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ የመቀበሪያ ቦታቸውም ከመኖሪያ ቤቱ ጓሮ ማሳ ውስጥ ሲሆን ቦታው እንዳይታወስ በቦታው እንሰት ይተከላል፡፡ አንድ ዓመት ለሞላቸውና ለአመት የተቃረቡ ሲሆኑ ግን በተወሰነ ደረጃ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ቢከናወንም ቀብሩም ሆነ ሀዘኑ ከአንድ ቀን እንደማያልፍ በጥናቱ ተገልጿል፡፡ በወጣትና በጎልማሳ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ደግሞ በተለይ ሳያገቡና ሳይወልዱ ለሚሞቱ ሀዘኑ የከፋ ታይቷል፡፡

እንዲሁም በጀግናና በጀግና ሚስት የሀዘን ሥነ ሥርዓት እንደታየው ሟቹ በመንደሩ በጀግንነቱ፣ በአስታራቂነቱና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚሳተፍ ከሆነ ለቅሶው ከሌላው በተለየ በብዙ ሰዎች የታጀበ ይሆናል፡፡ የጀግና ሚስትም ስትሞት በበሏ ጀግንነት ስለምትታወቅ ከሌላው ሰው የተለየ የሀዘን ሥነ ሥርዓት ይከናወንላታል፡፡ በሀድያ ማህበረሰብ እምነት ሞት የማይቀር ክስተት ቢሆንም የሰው ልጅ በምድር መኖር ያለበትን ዕድሜ ኖሮ መሞት እንደትልቅ እረፍት ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም የእድሜ ባለጸጋ ከሞተ መኖሪያ ቤቱ ፊት ለፊት በመቅበር የሚቹ ቤተሰቦች ሲወጡ ሲገቡ የመቃብር ቦታውን እያዩ ሁልጊዜ አብረው እንደሆኑና መንፈሱ እንደሚጠብቃቸው እንዲያስቡ እንደሚደረግ ከትንታኔው መረዳት ተችሏል፡፡

የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው በሀድያ ብሔረሰብ ለማህበራዊ ሕይወት መጠናከር ጉልህ ፋይዳ ካላቸው ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች አንዱ የሀዘን ሥነ ሥርዓት

[50] ቃለ መጠይቅ (ጥቅምት 18 ቀን 2012 ዓ/ም)፡፡

ሲሆን በእያንዳንዱ ሂደት በስነቃል፣ በቂስና በክዋኔ የሚተላለፉ መልዕክቶች የሀገረሰቡን ባህልና ታሪክ ለትውልድ የማሸጋገር እና ባህላዊ እሴቶች እንዲጠበቁ የማጠናከር፣ የማስተማርና የመቆጣጠር ተግባር እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

አለባቸው ኬሚሶና ሳሙኤል ሀንዳሞ፡፡ 2002፡፡ የሀድያ ህዝብ ታሪክና ባህል፡፡ አዲስ አበባ፡ ሰፊር አሳታሚ፡፡

አየለ መሎሬ፡፡ 1986፡፡ "የሀድያ ህብረተሰብ የለቅሶ ሥነ ሥርዓት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የቢ ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ 1992፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡ ባናዊ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡1993፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ 2009፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ አልፋ አሳታሚዎች አዲስ አበባ፡፡

Bauman, Richard. 1983. "The Field Study of Folklore in Context" In *A Handbook of American Folklore*, Journal of American Folklore pp. 362-367. Dorson R(Ed).

_______.(ed). 1992. *Folklore, Cultural Performance and Popular Entertainment*, New York: Oxford Univeresity press.

Bell, Catherine. 1997. Ritual Theory, Ritual practice. New York:Oxford University press.

Ben-Amos, Dan. 1993."Context in Context" <u>Theorizing Folklore towards New Perspective on the Politics of Culture,</u> Western Folklore.vol.52,No.2/4.

Brown, Corinne. 1963. *Understanding Others Culture*: Englewood Clffs: N.J.

Cohen, Milton. 1980. *Death Ritual: Antropological Perspectives*.Mcgraw-Hill Companies Inc.

Dorson, Richard.M. (ed). 1972. *Folklore and Folk life: An Introduction*. Chicago and London: the University of Chicago press.

Goldstein, Kenneth S. 1964. *A Guide for Field Workes in Folklore.* Folklore Associates INC. Hatboro, Pennsylvania: USA.

Hill, Jeff and Peggy Daniels. 2008. Life Events and Rites of Passege.Clifton D Bryant, Virginia Teach University.

Mazama, Ama and Molefikete Asante (eds). 2009. *Encyclopidia of African Relgion*. Sage Publications,Inc.

Rapaport, R. A. 1999. *Ritual and Relgion in the Marking of Humanity*. Combrige University Press.

Sims, Martha and Marthine, Stephens. 2005. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. United States of America, Utah University Press.

Solomon Mulugeta. 2008. *Socio Economic Base Line Survey of the Hadiya zone*.Childerens home society Family survices Ethiopia: Rohobot printer.

Van Gennep, Arnold. 1960. *The Rites of Passage*. Trans.M.B.Visedom and G.L. Caffee.Chicago Press.